# ከፍ የሚያደርጉ መቀመጫዎች



## ከፍ የሚያደርግ መቀመጫ የሚባለው ምንድን ነው?

ከፍ የሚያደርግ መቀመጫ መታጠቂያ የሌለው የመኪና ውስጥ መቀመጫ ወንበር ነው። ወንበሩ ልጁን ከፍ ስለሚያደርገው ሽንጥና ትከሻ ላይ የሚያርፈው ቀበቶ ልጁን በደንብ ይይዘዋል። ልጆች ይህን ከፍ የሚያደርግ ወንበር የሚጠቀሙት የመኪና ውስጥ መቀመጫ (ካር ሲት) የማይበቃቸው ሆነው ግን የአዋቂዎችን የደህንነት ቀበቶ ለመታጠቅ ትልቅ በማይሆኑበት ጊዜ ነው። በደንብ የማይገጥም የደህንነት ቀበቶ በግጭት ጊዜ ልጅዎን ከአደጋ አይከላከለውም። ውም።

## ልጄ ከፍ የሚያደርገውን መቀመጫ ለመጠቀም የሚደርሰው መቼ ነው?

ልጅዎ ለመኪና ውስጥ መቀመጫw የተሰጠው የቁመት ወይም የክብ ደት ገደብ ላይ እስኪደርስ ድረስ ፊቱን ወደ ፊት ለፊት አዙሮ የሚቀ መጥበት የመኪና ውስጥ መቀመጫ (ካር ሲት) ላይ በ5 - ነጥብ  ቀበ ቶ  ይሰሩት ( የአምራቹን መመሪያ ያንብቡ)። ልጆች ፊታቸውን ወደ ፊት ለፊት አድርገው ከሚቀመጡበት የመኪና ውስጥ መቀመጫ ት በላይ ሲያድጉ ከፍ በሚያደርገው መቀመጫ መጠቀም ይችላሉ። ል ጅዎ ከፍ በሚያደርገው መቀመጫ ለመጠቀም ቢያንስ 40 ፓውንድ የሚመዝን ሊሆን ይገባዋል።

በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ ልጆች 8 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ ወይ ም 4 ጫማ ከዘጠኝ ኢንች (57 ኢንች) እስኪደርሱ ድረስ ከፍ በሚያ ደርግ መቀመጫ እንዲጠቀሙ ሕጉ ያዝዛል። ዕድሜያቸው ከ13 ዓመ ት በታች የሆኑ ልጆች የሚቻል ሆኖ እስከተገኘ ድረስ መቀመጥ ያለባ ቸው በኋለኛው ወንበር ላይ ነው።

## ሽንጥ የሚደግፍ ቀበቶ ያለበትን ብቻ የመኪና ውስጥ መቀመጫ መጠቀም እችላለሁ?

አይቻልም። የመኪና ውስጥ መቀመጫዎች ጥቅም ላይ መዋል ያለባ ቸው ከሽንጥና ከትከሻ ቀበቶዎች ጋር መሆን አለባቸው።

- የኋለኛው መቀመጫዎ የመካከለኛ ማስቀመጫ የሽንጥ - ብቻ ቀ በቶ ካለው ፣ ከመኪና ውስጥ መቀመጫ ጋር የሽንጥና የትከሻ ቀ በቶ በሚጠቀሙበት የመኪና ውስጥ መቀመጫዎን በውጭ አቅ ጣጫ ያድርጉ።
- በኋላ በኩል ጥቅም ላይ የሚውል የሽንጥና የትከሻ ቀበቶ ከሌለዎት ፣ ከፍ የሚያደርገውን መቀመጫ የሽንጥና የትከሻ ቀበቶ ባለው ፊተኛው ወንበር ላይ አድርገው ይጠቀሙ። የፊተኛው ወንበር የተቻለውን ያህል ወደኋላ ይግፉት። መኪናዎ የአደጋ ጊዜ መከላከያ የአየር ከረጢት ካለው ያጥፉት።
- ሽንጥ ብቻ የሚደግፈውን ቀበቶ መጠቀም ግድ ከሆነ ልጅዎ ከፍ የሚያደርገውን ወንበር ሳይጠቀም ቀበቶውን ዝቅ አድርጎ ዳሌው ላይ ጠበቅ በማድረግ ሊያስረው ይገባል።

## ምን ዓይነት ከፍ የሚያደርጉ የመቀመጫ ዓይነቶች አሉ?

- የኋላ መቀመጫቸው ላይ የጭንቅላት ማሳረፊያ ያላቸው መኪኖች ውስጥ **መደገፊያ የሌለውን ከፍ የሚያደርግ መቀመጫ** መጠቀም ይቻላል። የልጅዎ ጭንቅላት ተመቻችቶ ትራሱ ላይ ማረፍ የማይችል ከሆነ ጭንቅላቱንና አንገቱን ከጉዳት ለመከላከል ሲባል ከፍ ያለ የኋላ መደገፊያ ያለውን ከፍ የሚደርግ መቀመጫ ይጠቀሙ።
- **የኋላ መደገፊያ ያለውን ከፍ የሚያደርግ መቀመጫ** የጭንቅላት ማሳረፊያ ትራስ ባላቸውም ሆነ በሌላቸው መኪናዎች ውስጥ መጠቀም ይቻላል።



መደገፊያ የሌለው ከፍ የሚያ ደርግ መቀመጫ



መደገፊያ ያለው ከፍ የሚደ ርግ መቀመጫ

### ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት

- www.800bucklup.org, 425-828-8975 ወይም 800-282-5587
- www.carsafekids.org
- www.safercar.gov
- www.seattlechildrens.org
- የልጅዎ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ

ሲያትል ችልድሬንስ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ይህንን መረጃ በሌሎች መልኮችም አዘጋጅቶ ያቀርባል። ለግብይት መገናኛዎች በስልክ ቁጥር 206-987-5205 ይደውሉ።

ይህ ጽሑፍ በሲያትል ችልድሬንስበሚገኙ የሕክምና ሠራተኞች ተገምግሟል። ይሁን እንጂ የእርስዎ ልጅ የሚያስፈልገው ነገር እንደየሁኔታው የተለየ ሊሆን ይችላል። ይህንን መረጃ ተመርኩዘው እርምጃ ከመውሰድዎ በፊት እባክዎ ከልጅዎ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ ጋር ይወያዩበት።

© 2004, 2007, 2010, 2011, 2014 Seattle Children's Hospital, Seattle, Washington. የባለቤቱ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።

7/14
CE484
(AMHARIC)